**ቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት በቶሮንቶ**
Kinijit Ethiopian Cultural and Relief Organization in Toronto
998 Bloor St West,, P.O.Box 10666, Toronto, ON  M6H - 1L8
**Tel./ Fax:  416 - 516 1244**

## ከቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት በቶሮንቶ የተላለፈ የደስታ መግለጫ መልዕክት

**ለቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ**
**አዲስ አበባ**

በሰኔ 14 እና 15 ቀን 2000 ዓ.ም **የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ጠቅላላ ጉባዔ እጅግ በደመቀና በተሳካ ሁኔታ በመጠናቀቁ የቅንጅት ድጋፍ ጽህፈት ቤት በቶሮንቶ የተሰማውን ደስታ ይገልጻል፡፡**

**ይህ ጉባዔ ቅንጅት ያጋጠመውን የውስጥ ችግር የመረመረበትና ያጠራበት፣ አባላቱ በተጠናከረ ሁኔታ ከመላው የሀገሪቱ ክፍሎች ተሰብስበው የመከሩበት፣ አንድ ሕዝብ መሆናቸውን ያረጋገጡበት፣ የፓርቲውን ደንብ ያሻሻሉበት፣ ብዙ ትላልቅ ውሳኔዎችን ያስተላለፉበት፣ አዲስ አመራር የመረጡበትና ስብሰባቸውን በድል ያጠናቀቁበት በመሆኑ ቅንጅት የያዘውን ራዕይና የተነሳበትን ዓላማ ከግቡ እንደሚያደርስ ማረጋገጫ በመስጠቱ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ተስፋ የሚሰጥና የሚያኮራ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም እንኳን ደስ አላችሁ እንኳን ደስ አለን እንላለን፡፡**

**የቅንጅት ኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት ጽህፈት ቤት በቶሮንቶ ለአዲሱ የቅንጅት አመራርና ለድርጅቱ አባላት ሁሉ የተቃናና የተሳካ መልካም የሥራ ዘመን እየተመኘ፤ ለምታደርጉት የነጻነትና የዲሞክራሲ ትግል የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነቱን እስከሚቀዳጅ ድረስ ከጎናችሁ መቆሙንና ድጋፉን የሚቀጥል መሆኑን ያረጋግጣል፡፡**

ሰኔ 17 ቀን 2000 ዓ.ም
**ቶሮንሮ፤ ካናዳ**

*Office Address:* 4 Westmoreland Ave. Toronto, Ontario M6H 2Z7 *(Bloor St.W. & West of Dovercourt)*